የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፭
አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

16th Year No. 15
ADDIS ABABA 5th March 2010


## ማውጫ


ደንብ ቁጥር ፩፻፸፬/፪ሺ፪
የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..... ገፅ ፭ሺ፪፻፯


## CONTENTS


Regulation No. 174/2009

Catering and Tourim Training Center Establishment Council of Ministers Regulation ............ Page 5207


**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፬/፪ሺ፪**
**የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከልን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ (በአዋጅ ቁጥር ፮፻፫/፪ሺ፩ እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፭ እና ፴፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ ‹‹የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፬/፪ሺ፪›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

፩. ‹‹ሚኒስቴር›› የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፤

፪. ‹‹ሞዴል ሆቴል›› ማለት ማዕከሉ በሥልጠና ወቅት ለተግባር መለማመጃ የሚጠቀምበት ሆቴል ነው፤

፫. ‹‹የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት›› ማለት

ሀ) የመኝታ፣ የምግብና መጠጥ ፣ የመዝናኛ እና መሰል አገልግሎቶችን፣ ወይም

ለ) የማስጎብኘት፣ የጉዞ ውክልና እና መሰል አገልግሎቶችን፣ የሚሰጥ ድርጅት ነው፤

፬. ‹‹ሰው›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፭. ማንኛውም በወንድ ፆታ የገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

*Council of Ministers Regulation No.174/2009*

***COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF CATERING AND TOURISM TRAINING CENTER***

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 (as amended by Proclamation No. 603/2008).

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Catering and Tourism Training Center Establishment Council of Ministers Regulation No. 174/2009".

2. **Definitions**

In this Regulation unless the context requires otherwise:

1/ "Ministry" means the Ministry of Culture and Tourism;

2/ "model hotel" means a hotel used by the center for demonstration in the course of training;

3/ "tourist service rendering organization" means an organization that:

a) provides accommodation, catering, recreation, and similar services; or

b) renders tour guidance, travel agency, and similar services:

4/ "person" means any natural or juridical person;

5/ any expression in the masculine gender includes the feminine.


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 3.60

፫. መቋቋም

፩. የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል (ከዚህ በኋላ ‹‹ማዕከል›› እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል::

፪/ የማዕከሉ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል::

፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የማዕከሉ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል::

፭. ዓላማ

ማዕከሉ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የቱሪዝም ኢንዱስትሪን ዕድገትና ልማት ለማፋጠን የሚያስፈልገውን በጽንሰ ሐሳብና በተግባር የሰለጠነ የሰው ኃይል በጥራትና በብቃት ለማፍራት የቅድመ ሥራ ስምሪት ሥልጠና መስጠት፤

፪/ በቱሪዝም ኢንዱስትሪ ለተሰማሩ የሥራ ኃላፊዎ ችና ሠራተኞች የአጭርና የረዥም ጊዜ የሙያ ማሻሻያና የሥራ ላይ ሥልጠና መስጠት፤

፫/ በሆቴልና በቱሪዝም ሙያ ጥናትና ምርምር ማካ ሄድ፣ በዘርፉ የልዕቀት ማዕከል በመሆን ለመሰል ተቋማት የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት፤

፬/ ለቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች አስፈላጊ ውን የምክር አገልግሎት መስጠት::

፮. የማዕከሉ ሥልጣንና ተግባር

ማዕከሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩ ታል:-

፩/ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅዶችን በማውጣት ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ የሚያስፈ ልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የቅ ድመ ሥራ ስምሪት እና የሥራ ላይ ሥልጠና ይሰጣል፤

፪/ ለሆቴልና ቱሪዝም መስክ እድገትና ልማት ጠቃሚ የሆነ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ ግኝቶችንም ያሠራጫል፤

፫/ ለቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

፬/ በሆቴልና ቱሪዝም መስክ በዓበይትና ወቅታዊ ጉዳዮች፣ በምርምር ውጤቶችና አዳዲስ አስተሳ ሰቦች ላይ ሴሚናሮችን፣ ሲምፖዚየሞችንና ወርክ ሾፖችን ከሚመለከታቸው ጋር በመተባ በር ያዘጋጃል፤

፭/ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ሞዴል ሆቴሉን ይቆጣ ጠራል፣ የአገልግሎት ጥራቱንም ያሳድጋል፤

3. Establishment

1/ The Catering and Tourism Training Center (hereinafter the "Center") is hereby established as an autonomous federal organ having its own legal personality.

2/ The Center shall be accountable to the Ministry.

4. Head Office

The Center shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices in other places, as may be necessary.

5. Objectives

The Center shall have the following objectives:

1/ to give pre-service training to produce the required number of adequately trained manpower, combining theory and practice, in order to enhance the growth and development of the tourism industry;

2/ to provide short and long term skill upgrading and on-the-job training for the management and employees working in the tourism industry;

3/ to undertake studies and research in the field of hotel and tourism; to be center of excellence in the sector and provide capacity building support to similar institutions;

4/ to provide consultancy services to tourist service rendering organizations.

6. Powers and Duties of the Center

The Center shall have the powers and duties to:

1/ on the basis of short, medium and long term plans, give pre-service and in- service training to produce skilled manpower required by the tourism industry;

2/ undertake studies and research to enhance the growth and development of the hotel and tourism sector, and disseminate the findings thereof;

3/ provide consultancy services to tourist service rendering organizations;

4/ organize, in cooperation with concerned bodies, seminars, symposiums and workshops on major current issues, research findings and new concepts related to the hotel and tourism sector;

5/ supervise, in accordance with the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992, its model hotel and enhance the quality of its services;

፮/ በዘመናዊ ቴክኖሎጂና በሌሎች ዘዴዎች እየተገለገለ አቅሙን በመገንባት የስልጠና ብቃቱን ያሻሽላል፤

፯/ በሃገር ውስጥና በሌሎች ሃገሮች ከሚገኙ ተመሣሣይ ዓላማ ካላቸው ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነት ይመሠርታል፤

፰/ ለሚሰጣቸው የሥልጠና እና የምክር አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ዋጋ ያስከፍላል፤

፱/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

፲/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስየሚያስፈልጉ ሌሎች ህጋዊ ተግባራትን ያከናውናል::

**፯. የማዕከሉ አቋም**

ማዕከሉ፡-

፩/ የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፣

፪/ በመንግሥት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣

፫/ አካዳሚክ ጉባዔ፣ እና

፬/ አስፈላጊው ሠራተኞች፣ ይኖሩታል::

**፰. የቦርድ አባላት**

ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል:: ቁጥራቸውም እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል::

**፱. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩/ የማዕከሉን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤

፪/ የማዕከሉን መዋቅርና የሥራ መመሪያዎችን ያፀድቃል፤

፫/ የማዕከሉን ዓመታዊ የሥልጠናና የሥራ ፕሮግራም፣ የአጭርና የረዥም ጊዜ እቅድ እንዲሁም በጀት መርምሮ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ በሚኒስቴሩ አማካይነት ለመንግሥት ቀርቦ የፀደቀው ዕቅድ፣ በጀትና ፕሮግራም በማዕከሉ ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፤

፬/ የማዕከሉን ሥራ አፈፃፀም ሪፖርት እየገመገመ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

፭/ የማዕከሉን ሥልጠናና የአካዳሚክ መመሪያዎችን ያፀድቃል፤ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፮/ ማዕከሉ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ካሉ መሰል ተቋሞች ጋር የሚያደርጋቸውን ስምምነቶች መርምሮ ያፀድቃል::

6/ develop its training capability by building its capacity through the use of modern technology and other means;

7/ establish relationship with local and foreign institutions that have similar objectives;

8/ charge commensurate fees for the training and consultancy services it renders;

9/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

10/ carry out other lawful activities necessary for the attainment of its objectives.

**7. Organization of the Center**

The Center shall have:

1/ a Management Board (hereinafter the "Board");

2/ a Director General and a Deputy Director General to be appointed by the Government;

3/ an Academic Council; and

4/ the necessary staff.

**8. Members of the Board**

Members of the Board, including the chairperson, shall be designated by the Government, and their number shall be determined as may be necessary.

**9. Powers and Duties of the Board**

The Board shall have the powers and duties to:

1/ oversee the activities of the Center;

2/ approve the organizational structure and working manuals of the Center;

3/ review and submit to the Ministry, for government approval, annual training programmes, short and long term plans and budgets of the Center, and ensure the implementation of the same upon approval;

4/ evaluate and submit to the Ministry performance reports of the Center;

5/ approve the Center's training and academic manuals and monitor their implementation;

6/ examine and approve agreements reached between the Center and similar local and foreign institutions.

## ፲. የቦርዱ ስብሰባ

፩/ ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል::

፪/ ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል::

፫/ የቦርዱ ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሀሳብ የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል::

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል::

## ፲፩. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የማዕከሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የማዕከሉን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል::

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ዳይሬክተር:-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የማዕከሉን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ ዓላማ ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የማዕከሉን የአካዳሚክ ሠራተኞች እንዲሁም በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ሌሎቹን የማዕከሉን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የማዕከሉን ዓመታዊ ሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ በመንግሥት ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለማዕከሉ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል:-

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ማዕከሉን ይወክላል፤

ረ) የማዕከሉን አካዳሚክ ጉባዔ በሰብሳቢነት ይመራል፤

## 10. Meetings of the Board

1/ The Board shall meet once a month; provided, however, that it may meet at any time where necessary.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members of the Board are present at any meeting.

3/ Decisions of the Board shall be passed by majority votes; in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may adopt its own rules of procedures.

## 11. Powers and Duties of the Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Center and shall, subject to the general directives of the Board, direct and administer the activities of the Center.

2/ Without limiting the generality stated under sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Center stated under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer the academic staff of the Center in accordance with directives to be approved by the Government following the basic principles of the federal civil service laws, and other employees of the Center in accordance with the federal civil service laws;

c) prepare and submit to the Board annual work plans and budgets of the Center, and implement the same upon approval by the Government;

d) effect payments in accordance with the approved budget of the Center;

e) represent the Center in all its dealings with third parties;

f) preside over the meetings of the Academic Council of the Center;

ሰ) በቦርዱ ስብሰባዎች ላይ ድምፅ የመስ ጠት መብት ሳይኖረው ይሳተፋል፤

ሸ) የማዕከሉን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

ቀ) በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል::

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለማዕከሉ ሥራ ቅልጥፍና ባስፈ ለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች የማዕከሉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል::

**፲፪. የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ:-

፩/ የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤

፪/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል::

**፲፫. የአካዳሚክ ጉባዔው አባላት**

የማዕከሉ አካዳሚክ ጉባዔ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል:-

፩/ የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር.......... ሰብሳቢ

፪/ የማዕከሉ ምክትል ዋና ዳይሬክተር...... አባል

፫/ የማዕከሉ የትምህርት ዲፓርትመንት ኃላፊዎች........አባላት

፬/ የማዕከሉ ሬጂስትራር ......አባል

፭/ በማዕከሉ ቋሚ መምህራን የሚመረጡ ሁለት (አንድ ሴት) የመምህራን ተወካዮች ........አባላት

፮/ በማዕከሉ ተማሪዎች የሚመረጡ ሁለት (አንድ ሴት) የተማሪዎች ተወካዮች ...................... አባላት

**፲፬. የአካዳሚክ ጉባዔው ሥልጣንና ተግባር**

የማዕከሉ አካዳሚክ ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል:-

፩/ የማዕከሉን የአካዳሚክ መመሪያ ያዘጋጃል፤ በቦርዱ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪/ የማዕከሉን የሥልጠና ፕሮግራሞች እየመረመረ እንዲፀድቁ ለቦርዱ ያቀርባል፤

፫/ ማዕከሉ አዲስ የሥልጠና መስክ ለመጀመር ወይም ያለውን ሥርዓተ ትምህርት ለማሻሻል ሲያቅድ ይዘቱን መርምሮ እንዲፀድቅ ለቦርዱ ያቀርባል፤

፬/ የማዕከሉን አካዳሚክ ካሌንደር መርምሮ ያፀድቃል፤

፭/ የሠልጣኞችን ፈተናና ምዘና በተመለከተ መመሪያዎችን ያወጣል፤ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤

g) attend meetings of the Board without having voting rights;

h) prepare performance and financial reports of the Center and submit to the Board;

i) perform such other duties as may be given to him by the Board.

3/ The Director General may, to the extent necessary for the efficient performance of the Center, delegate part of his powers and duties to other officials and employees of the Center.

**12. Powers and Duties of the Deputy Director General**

The Deputy Director General shall:

1/ act on behalf of the Director General in his absence;

2/ perform such other duties specifically given to him by the Director General.

**13. Members of the Academic Council**

The Academic Council of the Center shall have the following members:

1/ the Director General of the Center ----- Chairperson

2/ the Deputy Director General of the Center ----- Member

3/ heads of educational departments of the Center - Members

4/ the registrar of the Center ------------- Member

5/ two (one female) teachers' representatives elected by permanent academic staff of the Center --------- Members

6/ two (one female) students' representatives elect ed by the students of the Center ------ Members

**14. Powers and Duties of the Academic Council**

The Academic Council shall have the following powers and duties to:

1/ prepare the Centers academic rules and regulations, and implement the same upon approval by the Board;

2/ review the training programs of the Center and submit the same to the Board for approval;

3/ review the Center's plans for the introduction of new courses or the revision of its curriculum and submit the same to the Board for approval;

4/ review and approve the academic calendar of the Center;

5/ adopt guidelines for examining and assessment of trainees, and follow up their implementation;

፮/ በየሴሚስተሩ፣ በየዓመቱና በየኮርሱ ማጠቃለያ የሰልጣኞችን የትምህርት ውጤትና ደረጃ ይገመግማል፤ የተመራቂ ሰልጣኞች ውጤት መርምሮ ያጸድቃል፤

፯/ ለሰልጣኞች ሠርቲፊኬት፣ ዲፕሎማና ሽልማት የሚሰጥበትን ሁኔታ ያጠናል፤ በቦርድ ሲፈቀድም ተግባራዊ ደርጋል፤

፰/ ለማዕከሉ መምህራንና ሠልጣኞች የሥነ ምግባር መመሪያ ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፱/ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፤

፲/ ሌሎች በቦርዱ የሚሰጡ የአካዳሚክና የሥልጠና ጉዳዮችን ያከናውናል።

**፲፭. በጀት**

የማዕከሉ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል:-

፩/ በመንግሥት ከሚመደብለት በጀት፤ እና

፪/ ከሥልጠናና ከምክር አገልግሎት የሚገኝ ገቢ።

**፲፮. ስለሂሣብ መዛግብት**

፩/ ማዕከሉ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የማዕከሉ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም በእርሱ በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

**፲፯. የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በመባል የሚታወቀው አካል መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለማዕከሉ ተላልፈዋል።

**፲፰. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

6/ evaluate the academic results and ranks of trainees at the end of each semester, year and course; review and approve the results of graduating trainees;

7/ undertake studies of the conditions of issuance of certificates, diplomas and prizes to trainees, and implement the same upon approval by the Board;

8/ formulate code of ethics for teachers and trainees of the Center, and implement the same upon approval;

9/ adopt its own rules of procedure;

10/ perform such other academic and training activities as may be given to it by the Board.

**15. Budget**

The Center's budget shall be drawn from the following sources:

1/ budgetary appropriations by the Government; and

2/ fees charged for training and consultancy services.

**16. Books of Accounts**

1/ The Center shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Center shall be audited annually by the Auditor General or by auditors designated by him.

**17. Transfer of Rights and Obligations**

The rights and obligations of the organ known as the Catering and Tourism Training Center are hereby transferred to the Center.

**18. Effective Date**

This Regulation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa this 5th day of March, 2010.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA